Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# MCPS ለወላጆች/ለቤተሰቦች የጥናት ዘዴዎች

*ልዩ ድጋፍ ለሚሰጣቸው 3-21 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ተማሪዎች የማስጠናት ስልቶች*

**ልጅዎ እንዲማር፣ የራስ ጥረት እንዲገነባ የሚያግዙ ተሞክሮዎችን ያበልፅጉ፣ እና የዕድሜ ልክ የማጥናት ክህሎቶችን ያዳብሩ።**

እያንዳንዱ ልጅ በተለየ መንገድ መማር ይችላል። በልጅዎ IEP/504 እቅድ ላይ ስኬታማ ለመሆን የሚረዱ የድጋፍ አይነቶች ተለይተው ተቀምጠዋል። በቤት እና በትምህርት ቤት ወጥ የሆኑ የዕለት ተዕለት ተግባራት፣ ማበረታቻዎች፣ እና መግባባት ትምህርትን ያጠናክራሉ እንዲሁም በራስ መተማመንን ይገነባሉ። ትናንሽ የዕለት ተዕለት ተሞክሮዎች ትልቅ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ።

**ከትምህርት ቤቱ ጋር ግንኙነትዎን ይቀጥሉ**

**ከመምህራን፣ ጉዳይ ከሚከታተሉ አስፈጻሚዎች፣ እና ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር መደበኛ ግንኙነት ይኑርዎት። ስኬቶችን ያጋሩ፣ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ልጅዎ ወደ IEP ግቦች የሚያደርገውን/የምታደርገውን እድገት ለመደገፍ አብረው ይስሩ።**

### ዕለት ተዕለት የመማር ልማድ ይፍጠሩ

ለመማር፣ የቤት ስራ ለመሥራት፣ ለማንበብ ወይም ክህሎቶችን ለመለማመድ መደበኛ የሆነ ጊዜ እና ጸጥ ያለ ቦታ ያዘጋጁ። የትምህርት ቤት ግንኙነትን፣ የቤት ሥራዎችን፣ እና መጨ ተግባራትን በጋራ እየገመገሙ የተጠናቀቁ ተግባራትን ያድንቁ።

### ስራዎችን በመቀናነስ ይከፋፍሉ

ልጅዎ በአንድ ጊዜ አንድ እርምጃ እንዲያጠናቅቅ/እንድታጠናቅቅ ያግዙ። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ የሚታዩ መርሃ ግብሮችን፣ ማረጋገጫ ዝርዝሮችን፣ ሰዓት ቆጣሪ፣ ወይም የምስል ድጋፎችን ይጠቀሙ። ፍፁም የተስተካከለ ባይሆንም ጥረትንና የሚያሳየውን/የምታሳየውን እርምጃ ማወደስ ይገባል።

### በተናጠል የመሥራትን ፍላጎት ይገንቡ

ድጋፍ ከመስጠትዎ በፊት ልጅዎ ፕሮብሌሞችን እንዲፈታ/እንድትፈታ፣ ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ/እንድትጠይቅ፣ ምርጫዎችን መለየት እንዲችል/እንድትችል፣ እና እያንዳንዱን ተግባር በተቻለ መጠን ለብቻው(ዋ) ማጠናቀቅ እንዲችል/እንድትችል ያበረታቱ። በራስ መተማመን እያደገ ሲሄድ ቀስ በቀስ ድጋፍዎን ይቀንሱ።

### ራስን መደገፍ ያበረታቱ

ልጅዎ በተሻለ ሁኔታ መማር እንዲችል/እንድትችል የሚረዳውን/የሚረዳትን ነገር እንዲያውቅ/እንድታውቅ እና ድጋፍ ሲያስፈልግ መጠየቅ እንዲለማመድ/እንድትለማመድ ያድርጉ። ጥንካሬው(ዋ)ን፣ ተግዳሮቶችን፣ አኮሞዴሽኖችን፣ እና ግቦቹ(ቿ)ን እንደ እድሜው(ዋ) መጠን መገንዘብ እንዲችል/እንድትችል ያበረታቱ።

### የልጅዎን IEP/504 ድጋፎች በቤት ውስጥ ይጠቀሙ

**በትምህርት ቤት ውስጥ አመቺ የሆኑ አኮሞዴሽኖችን እና ስልቶችን ማዘጋጀት፣ ለምሳሌ፦**

- የእይታ ድጋፍ
- ጊዜ ማራዘም
- ተደጋጋሚ እረፍት
- አጋዥ ቴክኖሎጂ
- Assistive technology
- የስእል ማቀናበሪያ
- ከፍ ባለ ድምፅ ያንብቡ ወይም በንግግር መሳሪያ- አጭር ጽሑፍ - ያስተላለፉ
- ለመማር አማራጭ መንገዶች

### መማርን የዕለት ተዕለት ተግባር አድርጉት

**በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ክህሎቶችን ማዳበር ተለማመዱ፦**

- በየቀኑ አብራችሁ አንብቡ።
- ምግብ ሲያበስሉ ወይም ሲገዙ ይቁጠሩ፣ ይለኩ፣ እና ያወዳድሩ/ያነፃጽሩ።
- በውይይቶች፣ በጨዋታዎች፣ እና ታሪኮችን በመናገር ግንኙነትን ይገንቡ።
- ዕለት ተዕለት የኑሮ ዘዴን፣ ማደራጀት፣ ራስን መንከባከብ፣ እና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን አለማምዱ።
- በዕድሜ ትልልቅ ተማሪዎች ራስን የመደገፍ፣ የሙያ ዝግጁነት፣ እና ራስን የመቻል ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ያበረታቷቸው።

**ድጋፍ ይፈልጋሉ?**

**ከልጅዎ መምህር፣ ጉዳይ የሚከታተል/አስፈጻሚ፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የትምህርት ቤት ካውንስለር ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ጋር ትብብር ያድርጉ። በጋራ፣ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያድግ፣ እንዲማር እና ስኬታማ እንዲሆን መርዳት እንችላለን።**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች 2026